# <u>የቆሎ ተማሪና ኢትዮጵያዊነት</u>

## የቀሲስ አስተርአየ ጽጌ ንግግር በ<u>ኢሳት</u> የ3ኛ ዓመት ልደት ዝግጅት ላይ የቀረበ

ሰኔ ፳፯ ፳፻፩ ዓ.ም.

Silver Spring, Maryland, USA

በኢትዮጵያዊ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ካህናትርእዮት ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መሰረታውያን የሆኑትን ዓበይት ነገሮችን

- ፩ኛ ዘመን ያስቆጠሩትን ሶስቱ እምነቶች
- ፪ኛ የሚወራረሱባቸውን ጥቂት ነገሮች
- ፫ኛ ያሉበትን የጨለማ ዘመን
- ፬ኛ የእሳትን አስፈላጊነት ለማሳየት በቆሎ ታማሪነት ርእዮት ለማቅረብ እሞክራለሁ።

## <u>የቆሎ ተማሪ ኢትዮጵያዊነትን እንዴት ያየዋል?</u>

የቆሎ ተማሪ ኢትዮጵያን የሚመለከትበት ባህርዩን አብረን እንመልከት። የቆሎ ተማሪ ባህርዩ የተመሰረተው እየበላ፥ እየለበሰ፥ እያየ፥ ባደገበት ሁኔታዎች ላይ ነው። ኮፌደውን ይዞ ከጎጆው ወጥቶ እስኪመለስ ድረስ፤ በክንፍ የሚበሩትን፤ በደረታቸው የሚሳቡትን ፍጥረታት ሁሉ ይቃኛል። ሊፋለሙት በቁጣ ገስግሰው ወደሱ የሚመጡበትን የውሾችን ኃይል እየጣሰ ከማያውቀው መንደር ይገባል። (ከቤተ እስራኤላውያን፤ ከክርስቲያን ከሙስሊም መንደር ማለት ነው):: የሚሰጡትን ቁራሽም ሆነ ጥራጥሬ ሲቀበል ከሚሰጡበት እቃ ጀምሮ ወደሱ የሚንጸባረቀውን ርህራሄ ይመለከታል። ምግብ ብቻ ሳይሆን ለሰምና ወርቅ ለውስጠ ወይራ ለጎዳና እና ለሰርዝ ቅኔው የሚሆነውን ሀሳብ ከህዝብ ይሰበስባል። ይህን እያሰበ ብቻውን ሲጓዝ፤ ለሚመለከተው ሁሉ የአዕምሮ በሽታ ያለበት ይመስላል። ባላገሩ ግን ያውቀዋል።

## <u>የቆሎ ተማሪን ጠባይና ስሜት በቅጽልነት</u> <u>የሚጠራበት ምግቡ ይገልጸዋል</u>።

የማይቆረጠም ነገር መጉረስ ስለማይስማማው ምግቡ የቅጽል ስሙ የሚጠራበት ኮቸሮና <u>ቆሎ</u> ነው። እንጀራውንና ዳቦውን በፀሐይ አድርቆ ወደ ኮቸሮነት ይለውጠዋል።

ኮቸርና ቆሎ አይሻግትም። መንፈሱ እንደ እጀራ በቀላሉ የሚቀረስ እንደ ዳቦ የሚፈተት አይደለም። እንደ ገንፎ የሚዋጥ፤ እንደሙቅ የሚሰለቀጥ አይደለም። የቆሎ ተማሪ ባላፌ ጠፌ ነገር አይታለልም፤ አይጎመጅም።

ፎርማልና ኢንፎርማል የሚባሉ ሁለት ዓይነት መምህራንና የትምህርት ዘርፎች አሉት። ፎርማል መምህራን የቅኔና የመጽሕፍት ትርጓሜ መምህራን ናቸው።ኢንፎርማል መምህራኑ የቅኔው ባለቤት የአካባቢው ማህበረሰብ ነው። ኢንፎርማል ትምህርቱ በቅኔው የሚቃኛቸው <u>ክስተቶች</u> ናቸው።

## <u>የቆሎ ተማሪ ባህርዩና ርእዮቱም በልብሱ ይገለጻል</u>

ልብሱ ከበግ ቆዳ የተዘጋጀ ደበሎ ነው። የቆሎ ተማሪ ትምህርቱን ከሚመሰረትባቸው ብዙ ነገሮች አንዱ የሚለብሰው ደበሎ ነው። ደበሎ ዘመን በጨመረ መጠን፤ ወዝ እየጠገበ የበለጠ እየለፋ ሲሄድ ሰውነትን እየመሰለ፤ ከሰውነት ጋራ እየተስማማና እየጠነከረ ይሄዳል። የቆሎ ተማሪም እንደደበሎው በኢትዮጵያዊነት ስነልቦና ባህርይ እየታሸ፤ በኢትዮጵያዊነት ለዛ እየለሰለሰ ያድጋል። መታጠብ እንደማይፈልገው ደበሎው ጭንቅላቱ በማንም እንዲታጠብ አይፈቅድም። (ለምሳሌ በወያኔ ካድሬዎች ፕሮፓጋንዳ ወያም ጊዚያዊ ጥቅም አይታለልም)::

<u>እንደማያልቀው ደበሎው ከተናካሽ ውሾች ጋራ ከሚያደርገው ትግል ጀምሮ በወሰደው ትምህትና ልምድ ኢትዮጵያ በፈተና ላይ ስትወድቅ፤ ህዝቡም በመጣው ፈታና ሲደቅ፤ በረሀብ በበሽታ ሲያልቅ በሀሩርና በቁር ሰውነቱ ሲደርቅ በሚደረገው ትግል ሁሉ አብሮ ለመታሸት ለመልፋት ትእግስቱ አያልቅበትም</u>።

ማንኛውም የከብት ቆዳ ከከብቱ ጋራ በህይወት እስካለ ድረስ ለስላሳ (flexible) ነው። ተገፎ ከህይወት ከራቀ፤ ለምንም አይጠቅምም፤ ይገራል። ወደ ተፈለገ አገልግሎት ለመቀየር፤ በውሀ መነከር ፤በቅባት መልፋትና መታሸት አለበት። ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ካህን ለመሆን ከናትና ካባቱ ጉያ እየራቀ በመሄድ እድሜ ላይ ሲደርስ፤ በተፈጥሮ ምሥጢር ተነክሮ ይወጣ ዘንድ ቅኔ ቤት መግባት ግድ ነዉ:: ይህም በኢትዮጵያዊነት ግንዛቤ (civilized ወይም seasoned) ሆነ ማለት ነው።

ሊቃውንቱ፡- "በሙቀጫ ያልተፈተገ ገብስ፤
በቅኔ ያልታሸ ቄስ" አንድ ናቸው ይላሉ።

በሙቀጫ ካልተፈተገ ገብስ የሚጋገር እንጀራ ለመዋጥ እንደሚያስቸግር በቆሎ ትምህርት ያልታሸ ካህንም ለህብረተ ስብ ያስቸግራል።

የቆሎ ተማሪ ትእግስትና ጥንካሬ ያባ ወራወችን ስሜት ይማርካል። በኃይለኞች ውሻቸውና በተማሪው መካከል ያለውን የትግል ስልት ለመመልከት ተማሪው የሚመጣበትን ሰዓት የሚናፍቁ አባ ወራዎች ብዙ ናቸው። አንዳንድ ኢትዮጵያውያን አባ ወራዎች (አርበኞች) ከተማሪው ጋራ የሚታገለውን ውሻ "አይዞህ የኛ ጀግና በርታ! ይላሉ። ተማሪውንም፡- "ተሜ! ውሻ ሳትመታ፤ አንተም ሳትነከስ፤ ራትህን ይዘህ

**ለመውጣት ጥበብህን ተጠቀም"** ይሉታል። ይህ አባባል ሙሉ ቤት የሚያዘረፍ የቅኔ ምሥጢር ሙዳይ ነው።

በቆሎ ተመሪ ዘንድ ውሻ መምታት አይፈቀድም። ተማሪ ውሻውን ከመታ የቅኔ ተማሪነቱ ፈረሰ። ተሳስቶ ቢመታ፤ ታላላቆቹ እየታዘቡ ባይናገሩም የመንደሩ ጎረምሶች በይቅርታ አያልፉትም። ለዚህ ስነ ልቡና ለሚጠነቀቅ ተማሪ ጀግንነትን ከእውቀት ጋራ ያዋህደ፤ ለወደፊት ህብረተ ሰብ የሚጠቅም በሊቅ እና ባርበኝነት ይፈረጃል። ይህን የተመለከተ አባ ወራ ሳይቆረስ ሙሉ እንጀራ እንዲሰጠው ያዝዛል። አባቱ ለመሆን ራሱን ያጫል። የደረሰች ልጃገረድ ካለችውም ያጭለታል። ልጄን ድሬህ ባንድ በኩል ልጄ እንድትሆን፤ በክህነትህ ደግሞ ለኔም ላካባቢየም መምህረ ንስሀችን እንድትሆን አጭቸሀለሁ ይለዋል። ወደተወለደበት መንደር ሳይመለስም ይቀራል። አባ ወራዎችም ሆኑ የቆሎ ተማሪ በመንደር በጎሳና በቋንቋ የታሰሩ አይደሉም።

የቆሎ ተማሪ እንደ እሳት ከሚፋጁ ከውሾች ጋራ ከሚያደርገው ትግል ለመላቀቅ መውጫ መንገዶች ሁለት ብቻ ናቸው። አንዱ መፍትሄ ትምህርቱን ጥሎ መሸሽ ነው። ይህ የደካሞች መፍትሄ ነው። ጎበዝ ተማሪ ግን ርእዮቱን በምግቡና በደበሎው እንደቀረጸ፤ ከተናካሽ ውሾች በሚያገኘው የውጊያ ስልት ቅኔውን አብስሎ ወደ ዘራፊነት ደረጃ ለመድረስ መጣር ነው። ለሃይለኛ ውሻ የሚሰጠው ቅጽል እሳት ነው። ለጎበዝ ተማሪም የሚሰጠው ሌላው ቅጽል እሳት ነው።

አንድ እናት ቅኔ እንዲማርላት ልጇን ወደ ቅኔ ቤት ላከቸው በጎጆው እሳት ተነስቶ ተቃጠለ።

> "ይማርልኝ ብየ ቅኔ ቤት ሰድጄ
> ምሥጢር ገባው አሉ እሳት ሆነ ልጄ" ብላ አንጎራጎረችለት፤ ይባላል።

ጎበዝ ተማሪ በነዚህ ዓመታት ውስጥ እንደለበሰው ቆዳ ለፍቶ ታሽቶና ለስልሶ ዝግጁ ሲሆን ስሉጥ (civilized) ሆነ ይባላል። ይህም ማለት ከቆሎ ተማሪነት ለሰፊ አገልግሎት ተዘጋጀ፤ ወደ ዘራፊነት ተሻገረ ማለት ነው።

## በቆሎ ትምህርት ቤት እይታ ዘራፊነት ምንድ ነው?

በሶስት ምክንያቶች ዘራፊ የሚለው ቅጽል መጠሪያው ሆኖታል።

፩ኛ፦ ዘራፊው እንደ ተማሪው መንደር ለመንደር አይዞርም። በስሩ ያሉ አዳዲስ የቆሎ ተማሪዎች የእለት ምግቡን ያቀርቡለታል።

፪ኛ፦ የሚያስነግራቸው ከ ፲ ያላነሱ ተማሪዎቹ በተለያዩ አቅጣጫዎች ለልመና ከሚበተኑበት ያዩትንና የሰሙትን የህብረተ ህብረተ ሰቡን ሀሳብ እየሰበሰቡ ያመጡለታል።

፫ኛ፦ የሚያቀርቡለትን ሀሳብ መሰረት በማድረግ በተማሪነት ልምዱ እንደቀድሞው ሳይቸገር አዕምሮውን እያኳሸ (እያጋለ) ይዘርፋል።

ነገር ግን፤ ዘራፊነት ከዚህ ሲቀየር፤ ከቅኔ ምስጢር ክልል ሲያፈነግጥ ትርጉሙ ይቀየርና ይወይናል።(ጋጠ ወጥ፥ አጉራ ዘለል) ሆነ ማለት ነው።

ጥጋበኛ ወንበዴ ለህብረተ ሰቡ ጠቃሚ የኑሮ ትርጓሜ (ቅኔ) ሳያመነጭ፤ ህዝቡ ጥሮ ግሮ የሰበሰበውን ንብረት መዝረፍ ይጀምራል። (እንደ ዘመኑ መንግስት ዓይነት ማለት)። የቆሎ ተማሪ ይህንን መወየን ይለዋል። የኢትዮጵያዊ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ክህነት በቆሎ ትምህርት ቤት ታሽቶ በተዛመደ ኢትዮጵያዊነት ላይ ከተመሰረተ፤ በኢትዮጵያዊነት ግንዛቤ ህብረተ ሰቦች እየተረዳ፤በአገራችን ውስጥ ያሉትን የታላላቅ ሃይማኖቶች ግንኙነቶች በፖለቲካል ሳይንስ ከረቀቀ ሊቅ ባላነሰ አንክሮና ተዘክሮ ይመለከታቸዋል።

በቤተ ክርስቲያን ቆሎ ተማሪ ቤት ተቀርጾ ያደገ ካህን ህብረተ ሰቡ በፈተና ማእበል ላይ ሲወድቅ “ ሂጅ አገርሽ ግቢ ተመለሽ ቅኔ፥

ወንዶች በዋሉበት መዋሌ ነው እኔ” ብሎ ከተናካሽ ውሾች የተማረውን እሳትነት በመቀስቀስ፤ የህዝቡን ሰላምና ኑሮ ሊያደፈርስ በመጣ አጉራ ዘለልና ጋጠ ወጥ ሁሉ ላይ ይነሳበታል።

## ለቆሎ ተማሪ በሰላምና በፍቅር ገብቶ ዘመን ያስቆጠረን እምነት በያምንበትም ቅርሱ ነው።

የቆሎ ተማሪ፤ ታላላቅ እምነቶች ከመግባታቸው በፊት በአፍርሪካ ባህላዊ እምነት የነበሩትን ይመለከታል። ከዚያም ተከታትለው ወደ ኢትዮጵያ በመግባት ርስት ጉልት ይዘው የቆዩትን እምነቶች ይመረምራል።

ለምሳሌ፦

- ፩ኛ፦ አስቀድመው የመጡ የአይሁድ (ቤተ እስራዔላውያን) እምነት ተከታዮች
- ፪ኛ፡ ከአይሁድ እምነት ፈልቅቆ የወጣውን ክርስትናን የተቀበሉ ሰዎች
- ፫ኛ፦ በነቢያቸው ተሸኝተው በህዝባቸው ተሳደው ከነሱ በኋላ የመጡቱን ሙስሊሞች የተቀበላቸውን ኢትዮጵያዊነት ስሜትና አክብሮት ይመረምራል።

ሁሉም በተወለዱበት አገር ከፍቷቸው በመጡበት ጊዜ የተደረገላቸውን መስተንግዶ ያደንቃል። በዚህ ቅብብሎሽ ወደ ቅድስት ኢትዮጵያ የመጡ ጥንታውያን፤ አሁን የተረከብናትን ኢትዮጵያን በእምነትና በሌላም እያሳበቡ በመግባት ለመበታተን ከሚሞክሩት ጠላቶች በመከላለል እስከኛ ድረስ ማድረሳቸውን ያደንቃል። የራሱ ታሪክ እንደሆነ አድርጎም ይቀበላል።

ሁሉም እምነቶች በነገረ መለኮት ግንዛቤያቸው ቢለያዩም፤ በሴማቲክ ስሜታቸው የሚመሳሰሉበትና የሚከባበሩበት ቅርስነት አላቸው።

# የሚመሳሰሉበት

በቅኔ ቤት ግሳችን "ተሳለመ" ተፈቃቀረ፤ ተዋደደ፤ ተስማማ፤ በትህትና የሰላም እጅ በመዘርጋት ተቀባበለ። ሁላችንም በነገረ መለኮት ግንዛቤያችን መስመር በየ ቤተ ጸሎታችን "ዘአንሳእከነ እምድር ወአልአልከነ እመሬት"(ሥ ቅ ፱፡፳፩) "ከመሬት አፈር ሰው አርገህ ያበጀህን። ከመላእክት በላይ ያከበርከን" እያለን የምናስብበትን ራሳችንን መሬት እያስነካን መላ ሰውነታችንን በስግደት በአምልኮ ለፈጠረን አምላክ አናስገዛለን።

በሰባዊ ህብረታችን ደግሞ "ተሳለመ" ተፈቃቀረ ተዋደደ በሚለው መሰረት አንዳችን ላንዳችን ራሳችንን ዘንበል እያደረግን እጃችን ለሰላም እንዘረጋለን። እኛ ኦርቶዶክሳውያን ክርስቲያኖች "ሰላም ለኩልኩም" እያልን በንጀምረው ቅዳሴያችን "ተአምኍ በበይናቲክሙ በአምኃ ቅድሳት" እያለ እንቀጥልና፤ የህሊና መሰራረቅ ሽፍጥና ማስመሰል በሌበት በንጹህ ህሊና ና በልዑል ሞራል እጅ እንነሳሳለን። "ኦ ንጉሠ ሰላም ሰላመከ ሀበነ፤ ወአጽንዕ ለነ ሰላመከ" ብለን በምንደመድመው ቅዳሴያችን የሁላችንም ሰላም ሳይደፈርስ የሚያደፈርሰውንም በጋራ በመቋቋም እንድንታገል ቅዳሴያችን ይነግረናል። ዛሬ ግን ሁላችንም ከመሰላለም ወደ መስለምለም እንድንገባ ብዙ ግፌቶች እየተጫኑን ነው።

# ምንድ ነው መስለምለም?

መስለምለም ማለት "deteriorate"ማድረግ ነው።ዛሬ የወያኔ መንግሥት ክርስትናንም እስልምናንም ለማስለምለም ብዙ ጥረት እያደረገ ነው። ለምሳሌ ፀሐይ ወደ መግቢያዋ ስታዘነበል ብርሃኗ ይስለመለማል። ሰውም በከባድ በሽታ ላይ ሲወድቅ ይስለመለማል። ዛሬ መታረም የሚገባቸው የወየኑ አጉራ ዘለሎች ለነጻነት ላንድነት፡ ለሰላምና፡ ለምድራቸው የሚታገሉትን ሁሉ ታራሚ የሚል ቅጽል በመስጠት በእስር ቤት እያስለመለሙት ነው። ዛሬ ኢትዮጵያውያን ሁሉ በያሉበት፦

"ወይፈኑ ቢታመም ጊደሯም ታመመች
ኧረ ለመሆኑ ያች ስላም እንዴት ነች" የሚለውን ቅኔ እያንጎራጎሩ ናቸው።

በወያኔ መንግስት ሁሉም በመስለምለም ላይ ነው። ሁሉም ወደ ድቅድቅ ጨለማ እየገባ ነው። በምዕራቧ ለመጥለው በማሽቆልቆል ካለችው ፀሐይ ብርሃን በማጣት በዝግ ቤት እንዳለ ሰው ፤የኢትዮጵያ ህዝብ እሳቱን አንድዱት እያለ ነው።

## **<u>እሳት</u>**

**የቤተ ክርስቲያናችን አገላለጽ “እሳት ማህየዊ ለርቱአን ልብ እለ ይይገብሩ ፈቃዶ፤ እሳት በላኢ ለአማጽያን እለ ይክህዶ ስሞ” እንዲል፤ እሳት ሁለት ቅጽሎች አሉት። አንዱ በላኢ፤ ሌላው ማህየዊ (ታዳጊ) ነው። በበላኢነቱ ገለባወችን ጭራሮወች ግንዶችን እየተቃጠለ እያነደደ አመድና ከሰል ያደርጋቸዋል። በማህየዊነቱ “ርቱአነ ልብ” ቅን መንፈስ ያላቸውን እንደ ብረት ይግሉበታል። እንደ ብር ይነጥሩበታል እንደው ወርቅ ይፈልቁበታል።**

**በቤተ ክርስቲያን መመሪያ የተጻፈው “ወኢይኩን ገብረ ለአሐዱሂ እምሰብዕ እስመ እግዚአብሔር ዘወሀቦሙ ግእዛነ ኢይደሉ ከመ ይመንንዋ ለግእዛኖሙ”( ፍ አ ፱፡ ፫፻፩) ይላል። ማለትም፦ ሰዎች እግዚአብሄር የሰጣቸውን ነጻነት ማንም እንዲያስለመልምባቸው እንደ እሳት መንደድ መቃጠል መፋጀት አለባቸው። ሁላችንም እሳቱን የበለጠ ለማንደድ ሃይላችንን አቅማችንን ገንዘባችንን እያሰባሰብን ኦክሲጅንና ፊውል ለመሆን ሃላፊነት አለብን። ሁላችንም እሳቱን የበለጠ ለማንደድ ናፍ እየተገፋ እሳቱን የበለጠ የሚያንቀለቅል ኦክሲጅኖች መሆን አለብን። እንደገና ሁላችን በሚጎርፈው ኦክሲጅንና በእሳቱ መካከል ተጋድሞ ከግለት ወደ በለጠ ግለት እየናርን መሄድ አለብን እንደ ብር እየነጠርን እንደ ወርቅ እየፈለቅን መሄድ አለብን።**

**የሚሄደውን ብረት መሆን አለብን።<br>ኢትያጵያን እግዚአብሔር ይጠብቃት።**

***ለሌሎች ቀሲስ አስተርአየ ጽጌ ጦማሮች የሚከተለዉን ድህረ-ገጽ ይመልከቱ::***

http://www.medhanialemeotcks.org/